በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ
እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታና ወርሃዊ

# የአየር ጠባይ

# ግምገማ ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 1-31 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እና ከኖቬምበር 1-30/2024 የሚኖረው ወርሃዊ የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ - 1 -

ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 4 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት - 4 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 4 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 6 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 7 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ - 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-30፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 8 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ እና ሁለተኛው አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፉ ከመምጣታቸው ጋር በተያያዘ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ እንዲሁም በክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩትን የሀገሪቱ አከባቢዎችን ጨምሮ ዝናብ ማግኘታቸውን ቀጥለው ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም በኦክቶበር ሶስተኛው አሥራ አንድ ቀናት ወደ ወደ ሀገሪቷ ሲገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር ከዕለት ወደ ዕለት ከመጠናከሩ ጋር ተያይዞ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ወደ ሆኑት ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይም እንደተስፋፋና ዝናብ እንደነበራቸዉ እንዲሁም ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች አንጻራዊ መጠናከር በማሣየታቸው ምክንያት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበራቸው የደመና ሽፋን በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፣ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንዲኖር መንስዔ ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ በኦክቶበር ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች እንዲሁም በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የወቅቱ ዝናብ የቀጠለ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት እምብዛም ዝናብ የማይጠበቅባቸው የሰሜን፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይም በአንዳንድ አካባቢዎች ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደነበረ መረጃዎች ያመለክታሉ። በወሩ ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች ለመጥቀስም ያህል በአልጌ 66.0፣ በአንገር ጉቲን 45.6፣ በአዋሽ አርባ 40.0፣ በቡሬ 67.5፣ በጭፍራ 40.0፣ በዱብቲ 51.2፣ በፉኚዶ 73.6 እና 49.1 በጊኒር 75.6 በሀረር 52.0፣ በማጂ 84.3፣ በማንኩሽ 52.0 እና 84.6፣ በማሻ 44.5፣ በሞያሌ 46.0፣ በፓዌ 45.4፣ 40.6 እና 47.2፣ በሾላ ገበያ 43.3፣ በጉብሬ 46.2፣ በጉሊና 45.0፣ በጅማ 42.2፣ በቦሬ 57.0፣ ፣ በኢጃጂ 44.2፣ በላሬ 42.0፣ እንዲሁም በሳዉላ 53.0፣ በአማን 49.6፣ በአንገር ጉቲን 54.0፣ በዳንግላ 48.2፣ በደብረ ታቦር 40.7፣ በሆሳዕና 40.7፣ በሸርቆሌ 48.6፣ በሽላቦ 65.0፣ እንዲሁም በጭሮ 42.4 በሚ.ሜ የሚጠቀሱ ናቸው (ምስል 1) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፈው የኦክቶበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሃረርጌ ፤ ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ የፋፈን፣ የነጎብ፣ እና ኤረር ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች ከ81-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ13-30 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን ምስራቅ ሃረርጌ፤ እንዲሁም አፍዴር፣ ሸበል፣ ቆራሄ፣ ዶሎ፣ የኤረር፣ የጃረር ዞኖች ከ31-80 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-13 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው። በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኙዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከ81-410 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ13-30 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡

በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅና በደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የዋግህምራ፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ፣ የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ) እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤የምስራቅ፣ የምዕራብ የደቡብ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ የማሂ፣ አውሲ፣ ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ልዩ ዞን እና ሀላባ ዞን፤ በተጨማሪም ከሶማሌ ክልል የሲቲ ዞን፤ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ31-80 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ 5-16 ቀናት ያህል ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፤ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ፤ ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ የሸበል፣ የነጎብ፣ የቆራሂ፣ የዶሎ ዞኖች የሲቲ፣ የፋፈን፣ የኤረር፣ የጃረር፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡ በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኙዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ 31/2024
ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ 31/2024
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው
የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኦክቶበር ወር የነበረው የእርጥበት ሁኔታ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና በደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች በተለይም በቦረናና ጉጂ ዞኖች ለሚካሄደው መጠነኛ የሰብል ልማት የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ አጋማሽ በሚገኙ የሀገራችን አካባቢዎች ተጨማሪ እርጥበት ለሚያስፈልጋቸውና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ የመኸር ጊዜ ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም በዚህ ወቅት የተገኘው እርጥበት በተለይም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡

በሌላ በኩል በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት ዘግይተው ተዘርተው እድገታቸውን ላልጨረሱና ከመስከረም ወር መጀመሪያ ጀምሮ በአፈር ውስጥ በሚገኝ እርጥበት ለተዘሩ እንደ ሽንብራና ጓያ ላሉ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች እንዲሁም በአረንጓዴ አሻራ ለተተከሉ ተክሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር አዎንታዊ ጎን ነበረው፡፡ በአንጻሩ ግን በተለይም በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ እንዲሁም በአንዳንድ የመካከለኛው የሀገራችን አካባቢዎች የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው፣ (ካርታ 4)፡፡



ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው ወር በባሮ አኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቢ ሸበሌና አባይ እንዲሁም የላይኛውና መካከለኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በጥቂት የላይኛው ተከዜ፣ የላይኛው ምስራቃዊ አባይ እንዲሁም የታችኛውና የመካከለኛው ዋቢ ሸበሌ ኪስ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ተስተውሎባቸዋል፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ ለዘለቄ የዉሃ ሃብት ጥቅም እንደነበረው የተተነተኑ የዉሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የተቀሩት በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ የታችኛው አዋሽ እና ጥቂት የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ደረቃና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5) ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ከማመዘኑ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ የሚስተዋልበት ወር ነው፡፡ በሌላ በኩል በደቡብ አጋማሽና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናቡ እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

በሚቀጥለው የኖቬምበር ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀጣይነት እንደሚኖራቸዉና ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራል (ካርታ 6) ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-30፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የኖቬምበር ወር በተለይም የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ሊኖር የሚችለው እርጥበት በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና ፍርፍሬዎች እንዲሁም በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ለተተከሉ የተለያዩ የዛፍ ችግኞች የውኃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንሰሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ከፍተኛ ጠቀሜታ ከመኖሩም በተጨማሪ በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወታቸው በሆኑት አካባቢዎችና የበጋ ሰብል በሚያመርቱ እንደ ቦረናና ጉጂ ለመሳሰሉ አካባቢዎች ለሚኖረው የግብርና ስራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ወር የሚገኘው እርጥበት በተለይም



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን የሚፈጥር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ማህበረሰቡ እና የሚመለከታቸው አካላት ይህንን ለማከናወን የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። በአንጻሩ ግን የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን እና ሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አካባቢዎች ሊኖር የሚችለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ እንደ ሰሊጥ፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ አጃ እና ስንዴ እንዲሁም ቀድመው በሚደርሱ እንደ በቆሎ እና ማሽላ የመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው ስለሚችል አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት በየጣልቃው የሚኖረውን ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ መሰብሰብ ያስፈልጋል።

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኖቬምበር ወር በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ የታችኛው እና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የታችኛው አባይ እንዲሁም ጥቂት የኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የላይኛው አባይ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው አዋሽና ተከዜ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ የላይኛው ተከዜ እንዲሁም የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ ስር የሚቆይ ሲሆን በአንፃሩ ግን በቆላማ እና ውሃ አጠር በሆኑ ተፋሰሶች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ውሃን የመሰባሰብና የማጠራቀም ስራዎች እንዲሰሩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ከወዲሁ መስራት ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et